# የዚህ አመት የኔና የናንተ ውሳኔ

ሲራክ ከሚድ ዌስት

12/33/2010

“በአሮጌው” አመት መውጫና ባዲሱ አመት መግቢያ አካባቢ ይህን አደርጋለሁ ይህን አላደርግም ውሳኔዎች ማድረግ በብዙዎቻችን የተለመደ ሆኗል። ድሮ አገር ቤት ሆኜ ለመወፈር ውሳኔ በየአመቱ መግቢያ ላይ ውሳኔ ባደርግም ስከሳ እንጂ ክብድት የጨመርኩበት አመት አይታወሰኝም። ዛሬ ደግሞ ክብደት ለመቀነስ በያመቱ ቢያንስ ላላፉት በርካታ አመታት ውሳኔ ባደርግም ከመጨመር በስተቀር ውሳኔዬ አልሰመረልኝም። ያገር ቤቱ የክብደት መጨመር ውሳኔ ያልተሳካው ዋነኛውምክንያት ጥሩ ጥሩ ምግብ የመግዛት አቅሙ ስላልነበረኝ ነበር። በምድረ አሜሪካ የክብደት መቀነሱ አለመሳካት ግን ያቅም ጉዳይ ሳይሆን ቆራጥ ወኔ ማጣት ይመስለኛል።

# በቅድሚያ ግን እንኩአን ላዲስ አመት አደረሳችሁ!!

ለዚህ አመት ክብደት መቀነስን ሳልተው ሌሎች ግዙፍና ማህበራዊ የሆኑ ውሳኔዎችን አካትቼ በ365 ቀናት ውስጥ ራሴን ልፈትነው ተነስቻለሁ። ስለራሴ ሳወራ ለማጣቀሻ ያህል አንዳንድ ያንዳንድ ሰዎችን ወሬና ተግባር ስመረምር ያንዳንድ አንባቢዎችን ስሜት ብነካ ምክር እንጂ ርግማን አለመሆኑን ቢረዱልኝ መልካም እሆናል። ራሴንም ከመገሰጽ አላመልጥም።

2010 ለፓልቶክ እድገት ከፍተኛ አመት ሆኖ ሲሄድ መጭው 2011 እድገቱን ያፋጥናል እንጂ መሰናከል አይሆንበትም። በርግጥ ከፓለቲካው ይልቅ የሃይማኖትና የዋልጌዌች ቁጥር የፓልቶኩን መድረክ አጣቦታል። ካበሻው የፓልቶክ ክፍሎች የሱማሌዎቹ በየቀኑ ብጥፍ ይበልጣል። ምን ይሆን የሚያወሩት? ፓልቶክ ወደ ቪዲዮ ከኦንፍረንስ በመጭዎቹ ሁለትና ሰስት አመታት የሚሸጋገር ይመስለኛል፡፡ ለዚያ ስንደርስ እናየዋለን። ያሲሆን ግን ሁሉም አንደበቱን አረጋግቶ የጨዋ ሰው አነጋገር ይዞ ለመቅረብ መገደዱ አይቀርም።

እኔ በምወዳቸው ክፍሎች እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆኑ ትምህርቶችን ሲያስተምሩን የሚውሉትንና የሚያመሹትን ሰዎቸ አደንቃለሁ፡; አመስግናቸዋለሁ። ተግባራዊም ናቸው ብዬ እገምታለሁ። የዛኑ ያህል ደግሞ አብዛኛዎቹ የተግባር ሰዎች አይደሉም ተብለው ሲታሙም ሰምቻለሁ። ወሬኛ ካልሆኑ እሰየው ከሆኑ ደግሞ እንደኔ ራሳቸውን እንዲገመግሙና ያመቱንን ውሳኔአቸውን እንዲሰጡ እመክራለሁ። ለመሆኑ ሁላችንም የምናደርገውን ነው የምናወራው ወይስ ለማውራት ብለን ነው የምናወረው? ያወራሁትን ተግባራዊ ለማድረግ ከራሴ ጋር ትግል ያደረኩበት ጊዜያቶች ብዙ ባይሆኑም አንዴም ቢሆን ተገቢ አይደለም። የሚጠበቅብኝም አይደለም። ስለመደራጀት ብዙ ብለናል። ወያኔን ለመጣል አማራጩ መደራጀት ነው ብለን እየሰበክን ራሳችን ያልተደራጀን ሰዎችን ቤቱ ይቁጠረው። በድርጅት ታቅፈናል የምንለውስ ለድርጅታችን ጥንካሬ ከምንሰጠው ግልጋሎት ይልቅ ለምንድነው ከወደ ወሬው የታደልነው? እንግዲያውስ ከዘንድሮው ውሳኔያችን አንዱ ሊሆን የሚገባው ያልተደራጀን እንደራጅ የተደራጀነው ደግሞ ጥርስ ያለው ስራ ለድርጅታችን እናበርክት የሚል ይሆናል።

ያለ ገንዘብ ድርጅትን ማንቀሳቀስ ዘበት ነው። ድርጅት ከሚጠይቀው አንዱ ጉዳይ መዋጮ በወቅቱ መክፈልን ነው። ያለገንዘብ የድርጅት አባል አይኮንም አልልን ምክንያቱም ስራ የሌላቸው የታመሙ ተማሪዎች እኔ በማቀው ድርጅት ውስጥ ያባልነት መብታቸው ሲከበር አያለሁና። ገንዘብ ከሌለህ ገደል ግባ የሚሉ ድርጅቶች አይኖሩም ከሚል ስህተትም ለመዘፈቅ አይቃጣኝም የመኖር መብት አላቸውና። የሆነ ሆኖ ግን ወራዊ መዋጮውን ለመግፋት ተራራ መውጣት የሚመስለው ጎበዝ ባንድ ምሽት የመንፈቅ እዳውን የሚከፍል ግብዣ ሲያደርግ ካላያችሁ ይሄው እየነገርኩችህ ነው። እንደዚህ አይነቱ ቁጥሩ ቀላል አይደለም። አንዳንዴ እኔንም ይቃጣኛል። ግን ስህተት መሆኑን ቀልቤ በቶሎ ስለሚነግረኝ ከዚህ አይነቱ ሞኝነት ቶሎ

ያወጣኛል። እና ለኔም የበለጠ ጥንካሬ ይሰጠኝ ዘንድ ለድርጅታቸው ልግስና የሚሰስቱ የዚህ አመት ውሳኔአቸው ለድርጅቱ መክፈል የሚገባኝን መዋጮ በወቅቱ እሰጣለሁ የሚል ውሳኔ ማድረግ አለባቸው። ለልጆቻችሁም ልደት የምታወጡትንም ወጭ ተገቢነት ባለው መንገድ አድርጉት። አንድ ልጅ ያለው ታጋይ ለልጁ ልደት ሶስት ቢስኪሌት መግዛት የለበትም። ልጁም አያስገድድም። እንዲህ አይነቱ የልጅ ፍቅር መግለጫ ለራሱ ለልጁ ግራም ያጋባዋል እኔንም ግራ እንደሚያጋባኝ ሁሉ።

ዛሬ ለዘመኑ እንዲያመች ተብሎ ቃሉ "መቻቻል"ተብሏል።ድሮማ   ሂስና ግለ-ሂስ እንለው ነበር። ዛሬ የተሰነዘረው ሃሳብ ትክክል አይደለም የተባለ ሰው ክብረህሊናው እነደተነካበት ያደርገውና ለድብድብ ይገላገላል። ስድቡም ወግ ያጣና የባለጌ አይነት ይሆናል መቼም የስድብ ወግ ባይነኖረውም። የሚተቸው ያቀረበው ሃሳብ እንጅ ሃሳቡን ባቀረበው ሰው ላይ አይደለም። ለምሳሌ ያህል እኔ "እባብ የዋህ" ነው ብል ሃሳቤን የሚቃም አንድ ሰው እባብ የዋህ አለመሆኑን ነው ማስረዳት ያለበት እንጅ እኔን እባብ ነህ ሊለኝ አይገባውም፡፡ አዳማጩም ግንፍለተኛውን ሰውዬ መገሰጽ አለባቸው። ሂስ ሊያቀርቡበት ይገባል። ተሳዳቢነውና ከሚሰድበኝ አፌን ልዝጋ ከሚል አባባል ከተኬደ ውይይቱ መልካም ሳይሆን ደካማ ይሆናል። እና ለመጨው አመት ውሳኔአችን መሆን ያለበት ሂስና ግለ-ሂስን ላዳብር መዘጋጀት የሚል ሊሆን ይገባል።

ለመሆኑ ስንቶቻችን ነን የምናነበው? እኔማ አንድ ያማርኛ መጽሃፍ ለማንበብና  ለመጭርስ ችግር እየገጠመኝ ነው:: እና ማንበብ ማንበብ ማንበብ መሆን ይገባዋል መፈክሩ። ምናልባትም ለሁሉም ድክመቶቻችን መፍትሄ ሊሆን ስለሚችል ማንበቡን በሚገባ መግፋት አለብን።  በወር አንዲት የእንግሊዝኛ ወይም ያማርኛ መጽሃፍ እንዴት ማንበብ ልቸገር በቀን አስር መጽሃፍ የሚወጣው ወሬ የምሰልቀው ጉድ? ቢያስቸግረኝም ይህ የማንበብ ጉዳይ አንዱ ያመቱ ውሳኔዬ ይሆናል።

# ላጠቃለውና የዚህ አመት የኔና የናንተ ውሳኔ መሆን ያለበት፡-

1. ድርጅቴን ከምኞት ባሻገር ላጠናክር ቃል እገባለሁ - ድርጅት የሌላችሁ መላምቱ

2. ለድረጅቱ ወረሃዊ መዋጪ በወቅቱ ልከፍል - በድረጅት ያልታቀፋችሁ እርዳታ ለማድረግ ከፈለጋችሁ የሚረደሩ ድረጅቶች በርካታ ናቸውና ለማን እንደምትረዱ ጥንቃቄ አድርጉ

3. ለሂስና ለግለ-ሂስ ልገዛ - ሃሳቡን እነጂ ግለሰቡን አንውቀጠው
4.
5. ላነብና ራሴን ላበስለው - የምናነበውን እንወቅና እናንብብ - ካስመሳይ ጸሃፊዎች ያውጣን
6.
7. የማይቀረውን ክብደት መቀነስ ተግባራዊ ላደርግ - ከ200 ወደ 180 ፓውንድ ለመውረድ -

## በተራ ቁጥር 5 ያለውን ማድረግ አለማድረጌን በ2011 መጨረሻ ልናየው ነው። አራቱን ግን ከነገ  ልጀምረው ነው። ደግሞም አደርገዋለሁ። እናንተስ?